የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት
ALL ETHIOPIA UNITY PARTY

☎ +251-111 55 35 06, +251-111 55 17 89, +251-116-55 12 56 Fax. +251-111 55 31 55
17013 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Abeba Ethiopia, Website:- www.kaeup.org e-mail:-ionq@ethionet.et

ቁጥር
Ref. No. 00213/766/02
ቀን
Date 01/10/02

የተከበራችሁ በአሜሪካ፣
በካናዳ፣
በአውሮፓ፣
በአስትሬሊያ እና በአፍሪካ
የምትገኙ ደጋፊዎቻችን

ጉዳዩ፡- <u>ምስጋና ስለማቅረብና የወደፊት አቅጣጫ ስለማመልከት</u>

ከሁሉ አስቀድሜ ባለፉት 18 ዓመታት አብራችሁን ለተጓዛችሁና ከዚያም ወዲህ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ፕሮግራም የራሳችሁ በማድረግ ለተቀላቀላችሁን እና ማናቸውንም የገንዘብ፣ የሞራል እና የሀሳብ ድጋፍ በማድረግ ከጎናችን ላልተለያችሁን ሁሉ ከፍተኛ ምስጋና ላቀርብላችሁ እወዳለሁ።

የምርጫውን ውጤት ከመኢአድ እና ከዓለም የተለያዩ ድህረ-ገጾች እንደተመለከታችሁት ሁሉ ገዢው ፓርቲ በሚያሳፍር ሁኔታ መቶ በመቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ድምፅ አግኝቼአለሁ ብሏል። ይህ ዝርፊያ ካልሆነ በቀር በምንም መለኪያ እውነተኛ ድምፅ መሆን አይችልም። ተገኘ የተባለው ድምፅ ከዚህ በታች እንደምናረጋግጠው የታቃዋሚ ፓርቲዎች በዋናነት በቂ ሥራ ባለመሥራታቸው ወይም ባሳዩት መከፋፈል ሳይሆን ገዢው ፓርቲ እና መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ በመናቅ በምርጫው ሂደትና በምርጫው ዕለት ማንኛውንም አይነት ተፅዕኖ በህዝቡና በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እጩ ተወዳዳሪዎች ላይ በፈፀሙት የፖለቲካ ፓርቲዎች ሥነ-ምግባር ጥሰት ነው። ገዢው ፓርቲ እና መንግሥት የፈፀሙትን ተጽዕኖዎች ከመራጮች፣ የሕዝብ ታዛቢዎች፣ የዕጩ ተወዳዳሪዎች እና የፓርቲ ታዛቢዎች ምዝገባ ጊዜ ጀምሮ እስከ ምርጫው ዕለት ያለውን መላውን ሂደት ማየት ይቻላል።

<u>የመራጮች፣ የሕዝብ ታዛቢዎች፣ የእጩ ተወዳዳሪዎች እና የፓርቲ ታዛቢዎች ምዝገባ</u>
ሕዝቡ በሚፈለገው ብዛት ካለመመዝገቡም በላይ የሕዝብ ታዛቢዎች ምዝገባ ወገናዊ ነበር። መምረጥ የሚችለው ሕዝብ ብዛት 38 ሚሊዮን ሆኖ ሳለ ተመዘገበ የተባለው ከ32 ሚሊዮን በታች ነው። ይኸም ሊመዘገብ ከሚችለው 84 በመቶው ብቻ መሆኑ በኩል ግን የገገርው ፓርቲ ካድሬዎች በቡድን በቡድን ተደራጅተው አንድ የቀበሌ ኃላፊ አምስት መራጮች ኢህአዴግን እንዲመርጡ ቤት ለቤት ሄደው ይመዘግቡ ነበር። እነዚህ የተመዘገቡት ሰዎች ኢህአዴግን እንዲመርጡ ግዴታ እንዲገቡ ተደረገ።

እያንዳንዱ መራጭ የገባውን ግዴታ እንዲያከብርም ሁለት ዋና ዘዴዎች ተጠቀሙ። ቡና እንዲጠጡ በእየቤቱና በእየ ቀበሌው ጽ/ቤት በመጥራት መራጩ ሕዝብ ነፃነቱን እንደ 1997ቱ ምርጫ እንዳይጠቀም የሥነ-ልቦና ጫና በማድረግ ኢህአዴግን እንዲመርጡ ተገደዱ።

በድምፅ መስጫ ቀን ከድምፅ ምርጫ ጣቢያዎች ጀምሮ እስከ 10 እና 15 ሜትር ርቀት ላይ የኢህአዴግ ካድሬዎች በቡድን በቡድን ሆነው በመቆም የመጣውን መራጭ በመቆጣጠር፣ ያልመጣውን ስልክ ደውለው በመጥራት፣ ኢህአዴግን እንዲመርጡ አድርገዋል። ይኸም በመሆኑ እንደ 1997ቱ ምርጫ ጊዜ ህዝቡ በፍላጎት እና በነፃነት ላይ የተመሠረተ ምርጫ ሊያደርግ አልቻለም።

የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ መመሪያ በኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ተረቅቆ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሀሳብ በሰጡበት መሠረት አልተፈጸመም። በተቃራኒው የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች ባልተሳተፉበት፣ የእያንዳንዱ ቀበሌ ሕብረተሰብ በቂ ቅስቀሳ ተደርጎለት ለስብሰባ ወጥቶ ባልጠቆመበትና የድጋፍ ሆነ የተቃውሞ ሀሳቡን ባልሰጠበት፣ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች ብቻ በተገኙበት የ2000 ዓ.ም የማሟያ ምርጫ ያገለገሉት ጥሩ ሥራ ሰርተዋል በመባል ዝርዝራቸው ቀርቦ እንዲፀድቅ በመደረጉ መኢአድ ድርጊቱን በመቃወም ባቀረበው ጥያቄ መሠረት እንደገና የሕዝብ ታዛቢዎች ምርጫ እንዲደረግ ስምምነት ተደርሷል። ቦርዱ ሁኔታዎች እንዲስተካከል ዳግመኛ የሕዝብ ተወካዮች ምርጫ ይደረጋል ቢልም በክልሎች ደረጃ ግን አልተደገመም። ተደገመ በተባለበት በአዲስ አበባ ከተማም በእየ ምክንያቱ ከገዢው ፓርቲ ተጽዕኖ ውጭ የሕዝብ ተዛቢዎች ምርጫ ዳግመኛ ሊከናወን አልቻለም። ይኸም በመሆኑ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ግንቦት 8 ቀን 2002 ዓ.ም ስለምርጫው ምልክት ትምህርት ይሰጥ በነበረበት ወቅት በጎደሉ የሕዝብ ታዛቢዎች ምትክ ሌሎች መመደብ አስፈልጎታል።

ሌላው ወሳኝ የምርጫ ጉዳይ የምርጫው ቀን ከመድረሱ በፊት 10 ቀን አስቀድሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች በእየ ወረዳው ላሉ የቦርዱ ሥራ አስፈፃሚዎች እንዲያስታውቁ የተጠየቁት የፖለቲካ ፓርቲዎች ታዛቢዎች ስም ዝርዝር ነው። ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች የታዛቢዎቻቸውን ስም ዝርዝር አስቀድሞ ለምርጫ ቦርዱ ሥራ አስፈፃሚዎች ማሳወቅ አባሎቻቸውን ለአደጋ እንደሚያጋልጥ በመስጋት በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ም/ቤት ተወያይተው መኢአድ ያለበት አንድ ኮሚቴ ተሰይሞ ቦርዱን በማነጋገር የስም ዝርዝራቸው የሚቀርብበት በአምስት ቀን እንዲቀነስ ተደርጓል። ይህም ሆኖ ለምርጫ ቦርድ በተሰጠው የፓርቲ ታዛቢዎች ስም ዝርዝር መሰረት ተወካዮቹ እየተጠሩ በማስፈራራት እና በዛቻ ሲባረሩ እምቢ ያሉ እንዲታሰሩ ተደርገው ከምርጫው በኋላ እንዲፈቱ ተደርጓል።

በዚህም ምክንያት ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ፣ በሁሉም ክልሎች ማለት ይቻላል፣ ምርጫው የመኢአድ እና የሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ታዛቢዎች በሌሉበት ምርጫው እንዲከናወን ተደርጓል። በገጠሩ ምርጫው ሲጀመር ኮሮጆው አልተፈተሸም ወይም እንዲቀየር ተደርጓል። በአዲስ አበባ ላይ ታዛቢዎቻችን የተገኙ ቢሆንም የተፈጸመው ተንኮል ተመሳሳይ ነው። ታዛቢዎቻችን በምርጫው ጣቢያ በተወሰነው ሰዓት ቢገኙም የገዢው ፓርቲ ተወካዮች እና የቦርዱ ሥራ አስፈጻሚዎች ብቻ ከሰዓቱ በፊት ተገኝተው የምርጫ ሂደት እንዲጀመር አድርገዋል። ታዛቢዎቻችን ድርጊቱን

ተቃውመው ለሥራ አስፈጻሚ ቢያስታውቁና ኮሮጀው እንዲፈተሽ ቢጠይቁም ሰሚ አላገኙም። በመሆኑም በመላ ሀገሪቱ ማለት ይቻላል የገገርው ፓርቲ ካድሬዎች እና የቦርዱ ሥራ አስፈጻሚ በሕብረት ኮሮጆውን እንዳሻቸው ሲሞሉትና ሲለውጡ ተስተውለዋል። ይህም በመደረጉ በምርጫ ዕለት ቆጠራ ሲደረግ ከተመዘገበው ህዝብ በላይ በትርፍነት የምርጫ ድምፅ በኮሮጆዎች ውስጥ ተገኝቷል ወይም ኮሮጆው ተቀይሮ በተፈለገው ድምፅ ተሞልቷል።

ከእጩ ተወዳዳሪዎች ምዝገባ በፊት በእየ ክልሉ ያሉ ሥራ አስፈጻሚዎቻችን ማስፈራራት፣ ዛቻ፣ ድብደባና እሥራት ደርሶባቸዋል። በሐዋ ዞን፣ በአፋርና በቤኒሻንጉል ክልሎች የታሰሩት እጩ ተወዳዳሪዎቻችን ከብዙ ውጣ ወረድ በኋላ ምዝገባው ከተጠናቀቀ በኋላ እንዲፈቱና እንዲመዘገቡ ተደርገዋል። ይሁን እንጂ ጠንካራ የሥራ አስፈጻሚ አባሎቻችን በታሰሩበት ሁኔታ፣ ምንም እንኳ የዕጩ ተወዳዳሪዎች ምልመላ ቀደም ብሎ የተጀመረ ቢሆንም፣ የምንፈልገውንና የምንችለውን የእጩ ተወዳዳሪዎች ብዛት ለምርጫው ለመመልመልና ለማስመዝገብ አልተቻለም። ይኸም ሆኖ በሁሉም ክልሎች በጠቅላላው 1516 እጩ ተወዳዳሪዎች ለማስመዝገብ ተሞክሮ ነበር። ከዚህ ውስጥ ለሀገር አቀፍ 401 እና ለክልል ምክር ቤት 1115 እጩዎች አቅርበን ነበር። ይሁን እንጂ በቋንቋ እና በዕድሜ በማሳበብ እንዲሁም ተገቢው መታወቂያ እያላቸው የላችሁም በማለት እንዳይመዘገቡ ከመደረጋቸውም በላይ የተመዘገቡትንም በማስፈራራትና በመደለል ከእጩነት እንዲገለሉ አድርገዋል። በዚህ ምክንያት 385 እጩ ተወዳዳሪዎቻችን ሳይመዘገቡ ቀርተዋል። ይህም ሆኖ በምርጫው ዕለት 347 ለሀገር አቀፍና 784 ለክልል ም/ቤት አስመዝግበናል። እነዚህ ሁሉ ቢያሸንፉ ኖሮ በሀገር አቀፍ ፓርላማ ከ 70 በመቶ በላይ መቀመጫ ሲኖረን፣ በክልል ደግሞ ከኦሮሚያ በስተቀር እንዲሁ 70 በመቶ በላይ የክልል ፓርላማ መቀመጫ በኖረን ነበር። እነዚህ አኂዞች በእርግጠኝነት ከፍተኛ አብላጫ ድምፅ በም/ቤቶቹ ስለሚሰጡን ጥሩ ሥራ መሥራት እንደሚቻል አያጠራጥርም።

<u>በቅስቀሳ ወቅት</u>

በቅስቀሳ ወቅት እጩ ተወዳዳሪዎቻችን በገጠሩ የሕግ ዋስትና መብታቸው ተጥሶ ህዝቡን ቀሰቀሳችኋል በመባል ተደብድበዋል፣ ታስረዋል። የእጩ ተወዳዳሪዎች ፎቶ ግራፍና የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባነሮች ከተለጠፉበት ተቀድደዋል። በእነዚህ ምክንያት እጅግ በጣም ብዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎቻችን ራሳቸውን በሚገባ ሊያስተዋውቁ አልቻሉም።

<u>በምርጫው ዕለት</u>

በምርጫው እለት በእየምርጫ ጣቢያዎች ለመራጩ ህዝብ የተደረገው መግለጫ ከዳር እስከ ዳር ኢህአዴግን ለማስመረጥ የታቀደ ነበር። በዚህ መሠረት (i) የምርጫ ወረቀቱ ላይ X ምልክት የኢህአዴግ ምልክት ላይ እንዲያሰፍሩ ይነገር ነበር፤ (ii) የምርጫ ቦታው ሚስጢራዊ ባለመሆኑ መራጮች ለመነጋገርና ለመተያየት ይችሉ ነበር፤ (iii) ሽማግሌዎችና አይነስውራን ሲመጡ የምርጫ ቦርድ ሥራ አስፈጻሚ አባላት ይመርጡላቸው ወይም ያግዙአቸው ነበር፣ (iv) በሚስጢራዊ የምርጫ ቦታ ኢህአዴግ የተመረጠበት የምርጫ ወረቀት ተቀምጦ ተገኝቷል፣ ይኸም ኢህአዴግን እንዲመርጡ የተነደፈ ዕቅድ ነበር። (v) አንዳንድ መራጮች ሁለትና ከዚያም በላይ የምርጫ ካርድ ይዘው ተገኝተዋል፤ (vi) በብዙ የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ኮሮጆ ተቀይሯል ወይም

ታዛቢዎች በምርጫ ቦታ ከመገኘታቸው እና ኮሮጀው ባዶ መሆኑ ሳይረጋገጥ አስቀድሞ ምርጫው እንዲጀመር ተደርጓል፤ ተቃውሞም ቢደረግ ሰሚ አልተገኘም። ከሁሉ በላይ ግን (i) በብዙ የምርጫ ጣቢያዎች የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ታዛቢዎች እንዳይገኙ ተደርጎ ምርጫው መከናወኑ፣ (ii) የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች በቡድን ተደራጅተው መራጩን ሕዝብ ለመመዝገብና ኢህአዴግን መምረጣቸውን ለማረጋገጥ ያደረጉት ቁጥጥር እና (iii) የፓርቲው ታዛቢዎች ከመገኘታቸው በፊት የምርጫ ኮሮጀው በድምፅ እንዲሞላ ወይም ኮሮጀውን ለመለወጥ የተደረገው ጥረት ለገዢው ፓርቲ መቶ በመቶ ድምፅ አግኝቼአለሁ ማለት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አብረክተዋል።

ከምርጫ ምዝገባና ቅስቀሳ ጊዜ ጀምሮ እስከ ምርጫው እለት በተፈጸሙ የሥነ-ምግባር ጥሰቶች መኢአድ የምርጫውን ሂደትና ውጤት ነፃና ፍትሐዊ አይደለም ብሎ እንዲደመደም ተገድዷል። በመሆኑም ውጤቱን እንደማይቀበል ለገዢው ፓርቲ፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ም/ቤት፣ ለብሔራዊ የምርጫ ቦርድ፣ ለአውሮፓ ሕብረት ታዛቢዎች፣ ለኢትዮጵያ አጋሮች ቡድንና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስታውቋል። ማስረጃም አስደግፎ ምርጫው እንዲደገም ጠይቋል[1]። መልስ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።

ካሁን በኋላ የመኢአድ አብይ ተግባር በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ጠቅላላ ሰብሰባ ጠርቶ ራሱን መገምገም ነው። ይህንንም እንዳደረገ እናሳውቃችኋለን። ለጊዜው ግን ከእናንተ ከደጋፊዎቻችን የምንጠብቀው ቀጣይ ድጋፍ አለ። እሱም በዓለም አቀፍ ደረጃ የምርጫው ሂደትና ውጤት ነፃና ፍትሐዊ እንዳልነበረ ማስረዳት እና ምርጫው እንደገና እንዲደገም ጫና መፍጠር አንዱ ሲሆን የአባላት ጠቅላላ ስብሰባ በእየደረጃው ተጠርቶ የወደፊቱን እስትራቴጂ መቀየስ አስፈላጊ በመሆኑ የተለመደውን የገንዘብ እርዳታ እንድታደርጉልን በትህትና እንጠይቃለን። ቢቻላችሁም በስብሰባችን ላይ የሚሳተፉ ተወካዩች እንድትልኩ ከወዲሁ በአክብሮት እንጋብዛችኋላን። መልሳችሁን በጉጉት እንጠብቃለን።

ዛሬም እንደ ትናንቱ ሰላማዊ ትግላችን ይቀጥላል! ነፃ፣ ፍትሐዊ፣ የበለፀገች እና የተከበረች ኢትዮጵያን በህብረትና በትግላችን እንገነባለን!

ከማክበር ሰላምታ ጋር

ያዕቆብ ልኬ
የመኢአድ ውጭ ጉዳይ ኃላፊ

[1] ለምርጫ ቦርድ የቀረበው ደብዳቤ እና አባሪ ማስረጃ ተጨማሪ መረጃ እንዲሆናችሁ ተያይዘዋል።